# አገር አቀፍ የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታ ለመወሰንና ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 547/2013

በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ባለሃብቶች በሚያስገቡት ጥሬ ዕቃና ወደ ውጭ የሚልኩትን ምርት ለማምረት የተጠቀሙት የግብዓት መጠን ወጥነት የሌለውና የግብዓት ምርት ጥመርታውን ለማወቅ የሚያስችል አሠራርና መመሪያ ባለመኖሩ ጥሬ ዕቃዎቹ ከውጭ በሚገቡበትና በሚወራረዱበት ጊዜ ችግር ሲያጋጥም በመቆየቱ፣

የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በተጠቃሚዎች በየጊዜው ቀርበው ለመወሰን የሚታየውን ውጣ ውረድና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በመቀነስ ለወጪ ንግዱ የተቀላጠፈ አገልግሎትና አሠራር ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

ለወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ፈጣን አገልግሎትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ወጥ የሆነ አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ለመወሰንና ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 547/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

1) "አዋጅ" ማለት የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ማለት ነው።

2) "አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ" ማለት አንድን የወጪ ምርት በተገለጸው መለኪያና መጠን ለማምረት የሚያስፈልግ የጥሬ ዕቃ ፍጆታ በተገለፀው መጠንና መለኪያ ማለት ነው ።

3) “የምርት ምድብ” ማለት ተቀራራቢነት ያላቸው የወጪ ምርቶችን የጋራ የመለያ ኮድ በመስጠት ስታንዳርድ የግብአት ምርት ጥመርታ የተዘጋጀላቸው የምርት ምድቦች ናቸው፡፡

4) “አገር አቀፍ ስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታ ኮሚቴ” ማለት ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተወጣጡ አባላት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቋቋመ አማካሪ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

5) “የቴክኒክ ኮሚቴ” ማለት በምርት ምድቦች ከሚመለከታቸውና ለምርቶቹ ቅርበት ካላቸው የመንግሥት ተቋማት በተወጣጡ አባላት የተቋቋመ በአገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅትና አፈፃፀም ላይ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ የሚሰጥ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

6) “የመላክ ግዴታ” ማለት በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለወጪ ምርቱ የተፈቀደውን ግብአት በመጠቀም ግብዓቱ የተፈቀደላቸውን የወጪ ምርቶችን በተወሰነው መጠን፣ በተወሰነው ጊዜ ወደ ውጭ የመላክ ግዴታ ማለት ነው፡፡

7) “ጥቅል ስም” ማለት አንድን የወጪ ምርት ለማምረት በአማራጭነት እና በተመሳሳይ መጠን ተተካክተው ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች የሚገለጹበት የወል ስም ማለት ነው፡፡

8) “ሁለገብ የግብዓት ዝርዝሮች” ማለት ባላቸው የአጠቃቀም ባህሪይና መተካካት ምክንያት በስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ውስጥ ያልተካተቱና እንደየምርት ምድቡ ምርቱን ለማምረት ከሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች የሲ አይ ኤፍ ዋጋ በመቶኛ ተሰልተው የሚፈቀዱ ግብዓቶች፣ አላቂ የምርት መገልገያ ዕቃዎችና አክሰሰሪ ማለት ነው፡፡

9) “ተለይቶ የተሰጠ ስም” ማለት የወጪ ምርቱን ለማምረት ለሚያስፈልገው ግብዓት ተለይቶ የተሰጠ የራሱ የሆነ መጠሪያ ማለት ነው፡፡

10) “ባለሥልጣን“ ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማለት ነው፡፡

11) “ሚኒስቴር“ ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

12) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታን በሁሉም የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች፣ አገር ውስጥ የሚመረቱ የሚገጣጠሙ የካፒታል እና ግንባታ ዕቃዎች ሽያጭ ላይ በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተፈቀደውን ተመላሽ ቀረጥ ለማስፈጸም፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እና ወጪ ምርቶችን ለማበረታታት ለሚውሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅት

4. አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ኮሚቴና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ስልጣን እና ተግባራት፡-

   1) አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ያዘጋጃል፣ እንዲፀድቅ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

   2) በተዘጋጀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ ላልተጠቀሱ አዳዲስ ወጪ ምርቶች እንዲሁም በተዘጋጀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመገምገም የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲፀድቅ ወይም እንዲሻሻል ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

   3) የተጨማሪ እሴት መጠን ሀሳብ ያቀርባል እና

   4) ሌሎች የሚሰጡ ተያያዥነት ያላቸው ስራዎችን ያከናውናል፡፡

5. በየወጪ ምርት ምድቡ የተቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች አዳዲስ የወጪ ምርቶች የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ እና በተዘጋጀው ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ የሚቀርቡ የማስተካከያ ጥያቄዎችን በመመርመር የሙያ አስተያየት ለአገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡

6. በተዘጋጀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ወይንም አዲስ ወደ ወጪ ምርት የሚገቡ ምርቶች የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲዘጋጅላቸው በማንኛውም የዘርፍ ማህበር፣ ድጋፍ ሰጪ ተቋም ወይንም የስርዓቶቹ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በማስረጃ በማስደገፍ ከማብራሪያ ጋር ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

7. ባለስልጣኑ የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታ ላልተዘጋጀላቸው ወይንም ተዘጋጅቶላቸው መሻሻል ለሚገባቸው ምርቶች በቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት እንዲገቡ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ በሚኒስቴሩ በተቋቋመው የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥምርታ ኮሚቴ ቀርቦ በሚወሰነው መሠረት ለመፈጸም ግዴታ እንዲገቡ በማድረግ ግብዓቶቹ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል።

8. በአንቀጽ 7 መሰረት ግብዓቶቹ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ሲፈቅድ አመልካቹ በተዘጋጀው የማመልከቻ ፎርም ለባለስልጣኑ ጥያቄውን በማቅረብ ለሚኒስቴሩ በግልባጭ ያሳውቃል፣ ባለሥልጣኑም ለግብዓት ምርት ጥመርታ ኮሚቴው ቀርቦ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመወሰን እንዲችል የማመልከቻውን ኮፒ በ7 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል።

9. አመልካቹ በሚወሰነው የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት ካልተጠቀመባቸው ወይም በልዩነት ለታዩ ግብዓቶች ቀረጡን ከነቅጣቱ የመክፈል ግዴታ አለበት። ሆኖም በግብዓቶቹ ሌሎች ወይንም ተጨማሪ ምርቶችን አምርቶ ወደ ውጭ ለመላክ ከፈለገ ባልተጠቀመባቸው ግብዓቶች ሌሎች ምርቶችን አምርቶ እንዲልክ አማራጭ ይሰጠዋል።

10. ኮሚቴው የቀረበለት መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ካመነና የግብዓት ምርት ጥመርታው ተጠቃሚው ካመለከተው መጠን በታች ነው የሚል ግምት ካለው ባለጉዳዩ ኮሚቴው ፊት ቀርቦ ሁኔታውን እንዲያስረዳ ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

11. ነገር ግን በአንቀጽ 10 መሠረት ቀርቦ ካላስረዳ በተመዘገበው አድራሻ ደብዳቤ ይፃፍለታል፣ ካልቀረበ እና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ ካልላከ በአዋጁ መሠረት ቀረጡን ከነቅጣቱ እንዲከፍል ይደረጋል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>አገር አቀፍ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታን ስለማጽደቅ</u>

12. የአገር አቀፍ የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታ የተዘጋጀላቸው 44 የወጪ ምርቶችን የያዘ የቆዳ ምርት ምድብ እና 360 የወጪ ምርቶችን የያዘ የጨርቃ ጨርቅ ምርት ምድብ በሚኒስቴሩ ፀድቆ በዚህ መመሪያ በሥራ ላይ ውሏል።

13. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የምርት ምድቦች እና የወጪ ምርቶች የአገር አቀፍ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ተዘጋጅቶላቸው በሚኒስቴሩ ሲፀድቁ በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ አተገባበር

14. በስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት ለወጪ ምርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ወይም ቀረጥ ተከፍሎባቸው በገቡት ላይ ተመላሽ ቀረጥ ለመጠየቅ፦

1) የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች በማበረታቻ ሥርዓቶቹ የሚያስገቧቸውን ወይንም ያስገቧቸውን ግብዓቶች ተጠቅመው የሚያመርቷቸውን ወጪ ምርቶች ታትሞ ከተዘጋጀው አገር አቀፍ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ወይንም ከሚኒስቴሩ ድህረ ገጽ ላይ የምርቱን መለያ ኮድ፣ የምርቱን ስም እና የሚያስገባውን ጥሬ ዕቃ ዝርዝር በመውሰድ ከማስገባቱ በፊት ወይም ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያቀርባል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የሥርዓቱ ተጠቃሚ በወጪ ምርቱ ሥር የተዘረዘሩት ግብዓቶች በሙሉ ወይም በከፊል ማስገባት ወይም ባስገባው ላይ ቀረጥ ተመላሽ መጠየቅ ይችላል፡፡

3) የወጪ ምርቱን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በጥቅል ስም ወይንም ተለይቶ በተቀመጠ ስም በስታንዳርዱ ያልተካተቱ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ **6** እና ለማሽኒያና መጠቅለያ ግብዓቶች አጠቃላይ መግለጫ አንቀጽ 16 በተገለፀው መሠረት አስፈላጊውን በሟሟላት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እንዲፈቀድላቸው ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

4) የአገር አቀፍ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታው ለአሠራር እንዲያመች በጥቅል ስም የተጠቀሱ ግብዓቶች ሲጠቀም አምራቹ የሚያስገባው ለወጪ ምርቱ አግባብነት ያለውን ግብዓት ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም የግብዓት ምርት ጥመርታው ለጥቅል ስም በአገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ከተቀመጠው መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

5) በስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታው በተገለፁ አንዳንድ የወጪ ምርቶች ሁለት ወይም ከሁለት በላይ አማራጭ ግብዓቶች ተመሳሳይ ምርት ለማምረት እንዲገቡ በተፈቀደባቸው ምርቶች ላይ አመልካቹ አንዱን አማራጭ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም አንዱን ዓይነት ምርት ለማምረት ከአንድ አማራጭ በላይ ግብዓት በሚያስፈልግበት ጊዜ አንዱን ዓይነት ምርት

በተለያዩ ግብዓት ዓይነቶች ማምረቱን የእያንዳንዱን ምርት መጠን ከእያንዳንዱ ግብዓት መጠን አንፃር በማስረዳት ማወራረድ ይኖርበታል፡፡

6) በየምርት ምድቡ በሁለገብ የግብዓት ዝርዝር የተጠቀሱት ግብዓቶች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ከተፈቀዱት ጠቅላላ ጥሬ ዕቃዎች ሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ በየምርት ምድቡ የተወሰነውን መቶኛ እስካልበለጡ ድረስ ከቀረጥ ነጻ ሊገቡ ወይም የቀረጥ ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

7) ወደ አገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀዱት ግብዓቶች በመጠን ተመዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡ ሆኖም ግብዓቶቹ በሠነዱ ላይ በዋጋቸው እንደወሳኝ ሁኔታ ተለይተው የሚወራረዱ ከሆነ ሲፈቀዱ በዋጋቸው ተለይተው መገለጽ አለባቸው፡፡ መጠናቸውና ዋጋቸው ሁለቱም ለማወራረድ ወሳኝ በሚሆኑበት ጊዜ እንደዚሁ በሁለቱም መገለጽ አለባቸው፡፡

**8)** በአገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ሠነዱ ላይ የግብዓት ምርት ጥመርታቸው የተጣራ ወይም የተጣራ መጠንና ብክነት በሚል የተጠቀሱት ግብዓቶች ላይ አምራቹ አንድን የወጪ ምርት ለማምረት የሚጠቀመው መጠን የተጣራ ፍጆታ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡ ሆኖም የቀረበው የግብዓት ምርት ጥመርታ ለባለሥልጣኑ ግልጽ ካልሆነ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት በቀረበው ጥያቄ መሠረት ከፈቀደ በኃላ ለውሳኔ ተሞልቶ የቀረበውን ቅጽ ኮፒ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፡፡

9) አምራች ላኪው ወይንም ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ከውጭ ያስመጣቸው ግብዓቶች ተጠቅሞ በማምረት ወደ ውጭ ለላካቸው ወይም ለቀጥተኛ ላኪዎች ያቀረባቸው ምርቶች በተዘጋጀው አገር አቀፍ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት ይወራረድለታል፡፡

## ክፍል አምስት

## የማሸጊያ ወይም የመጠቅለያ ዕቃዎች

15. በግብዓት ምርት ጥመርታ ለማሸጊያዎቻቸው እንደ ገቢ ግብዓቶች ላልተዘጋጀላቸው ወይም ተዘጋጅቶላቸው በግብዓት ምርት ጥመርታ ከተጠቀሱት ተጨማሪ ማሸጊያዎች ለሚያስፈልጋቸው የማሸጊያ ግብዓቶችን እንዲያስገቡ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚከተለው መሠረት ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

1) ባለቀላቸው መልክ የማሸጊያ ወይም የመጠቅለያ ዕቃዎችን ለሚያስገቡት የተጣራ መጠን ላይ 5% ብክነት በመጨመር፣

2) የማሸጊያ ወይም የመጠቅለያ ዕቃዎቹን ለማምረት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን ለሚያስገቡት የተጣራ መጠን ላይ 10% ብክነት በመጨመር የሚሰላ ይሆናል፣

3) የቀረበው የተጣራ የማሸጊያ መጠን ግልጽ ካልሆነ አመልካቹ ባቀረበው መሠረት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ከተፈቀደ በኋላ ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፣

4) ከላይ የተጠቀሱት የማሸጊያ ዕቃዎች በሚፈቀዱበት ጊዜ ለሁለገብ የግብዓቶች ዝርዝር ከተፈቀደው ጋር ተደምሮ ከቀረጥ ነፃ ከተገዙ ጥሬ ዕቃዎች ሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ አንፃር ተገናዝበው ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

17. የአገር አቀፍ የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታ ያልተዘጋጀላቸው ሌሎች የምርት ምድቦች የግብዓት ምርት ጥመርታ ተዘጋጅቶ በሚኒስቴሩ እስኪፀድቅ ድረስ ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

18. ቀደም ሲል በነበረው አሠራር ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት የግብዓት ምርት ጥመርታ የፀደቀላቸው እና ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ውለው ወደ ውጭ የተላኩ ጥሬ ዕቃዎች ቀደም ሲል በፀደቀው መሠረት የሚወራረዱ ይሆናል፡፡ ሆኖም መመሪያው በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የሚገዙ እና በክምችት ላይ ያሉ ግብዓቶች የሚስተናገዱት አዲስ በተዘጋጀው አገር አቀፍ የስታንዳርድ ግብዓት ምርት ጥመርታና በዚህ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

19. አዳዲስ የሚሰጡ ወይም የሚታደሱ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚነት ፈቃዶች አዲስ በተዘጋጀው አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት በሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

20. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

አህመድ አብተው

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

<u>አባሪ 1</u>

## <u>የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚዎች የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ያልፀደቀላቸውን ምርቶች/ግብዓቶች ወይንም የማሸጊያ ዕቃዎችን ወይንም በአጠቃላይ ግብዓት ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን ግብዓቶች ለማስገባት የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ</u>

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ____________________በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚነት ሴርተፊኬት ቁጥር ________ በቫውቸር ደብተር / ጉምሩክ ፈቃድ ቁጥር ______________________ ተጠቃሚ የሆንኩ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ለወጪ ምርቶች ግብዓትነት የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችን አላቂ የምርት መገልገያዎችን ማሸጊያዎችን ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫ፣ በገባሁት ግዴታና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኳቸው ቅጾች እና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት ጥሬ ዕቃዎቹ ተመዝግበው ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ፡፡

<u>ማረጋገጫ</u>

1. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ የወጪ ምርት ማሸጊያ/መጠቅለያ ዓይነት ኤክስፖርት ለማድረጋቸው ለተጠቀሱት ምርቶች የሚያስፈልጉ ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ወደ ውጭ በመላክ የማወራርድ መሆኔን፣

2. ጥሬ ዕቃዎቹ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ላልተዘጋጀላቸው የወጪ ምርቶች የሚያስፈልጉ ወይንም የተዘጋጀላቸው የወጪ ምርቶች ሆነው ግብዓቶቹ በአጠቃላይ ስም ወይንም ተለይቶ በተቀመጠ ስም በጥመርታው ያልተካተቱ ከሆኑ እስከ አንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከበቂ መረጃ ጋር የማቅረብና የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ የማስወስን መሆኔን፣

3. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ በሠንጠረዡ የተመለከተውን አንድን የወጪ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው መጠን ብቻ መሆኑን፣

4. የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን በመጠቀም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትንና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች የተቀመጡትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ---------------------------ስልክ ቁጥር------------ የድርጅቱ ስም---------------------

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ____________________

የአባሪ ገጽ ብዛት _____ ፊርማ ________________

የድርጅቱ ማህተም ______________________

አባሪ 2

## ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የተጠየቁት ጥሬ ዕቃዎች /ግብዓቶች ዝርዝር

ለማስገባት እንዲፈቀድላቸው የጠየቋቸው ግብዓቶች፡ ስ/ግ/ም/ጥ/ያልተዘጋጀላቸው ☐ ለማሸጊያ ዕቃዎች ☐

በጠቅላላ ዕቃዎች ዝርዝር ለተካተቱት ☐ ሌሎች ☐

| ተራ ቁጥር | የወጪ ምርት ዓይነት | የወጪ ምርቱ መለያ ኮድ | የወጪ ምርቱ መለኪያ | እንዲገቡ የተጠየቁት ጥሬ ዕቃዎች ዝርዝር | የጥሬ ዕቃዎቹ መለኪያ | አንዱን የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልግ ጥሬ ዕቃ መጠን | በምርት ሂደት የሚባክነው መጠን በ% | የግብዓት ምርት ጥመርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

* ፎርሙ ተሞልቶ ሁለቱ ከጥያቄው ጋር ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ይቀርባል የግ/ም/ጥ መወሰን ካለበት ከጥያቄ ጋር ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይቀርባል፣

* የገቢዎችና ጉምሩክ የቀረበው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ ግልጽ ያልሆነ ወይንም መወሰን ያለበት ከሆነ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይላካል፣